የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

☏ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251 116– 55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa, Ethiopia e-mail:-allethiopiaunityparty@gmail.com

ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

ቁጥር
Ref No. ____________
ቀን
Date____________

# በጭቆናና በአፈና ሥልጣንን ለማራዘም የሚካሔደው ዘመቻ ቀጥሏል!

## (በጉራፋርዳ የሚፈፀመው የሰብአዊ መብት ረገጣ እንዲቆም መኢአድ ይጠይቃል)

### ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ የተሰጠ መግለጫ

የመላው ኢትዮጵያ አንድት ድርጅት (መኢአድ) በኢትዮጵያ ውስጥ እየደረሰ ያለው የሰባዊ እና የዲሞክራሲ መብት እረገጣ ለማጋለጥ እና በተባበረ ክንድ ለማስቆም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ያለ ፓርቲ ነው። የኢህአዴግ ካድሬዎች በአገራችን ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ግድያ፣ እስራት፣ ቤት ማፍረስ፣ ከስራ ማባረር፣ የመሬት ንጥቂያ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጐን በመሆን ለማስቆም መኢአድ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

በጉራፋርዳ ወረዳ የሚፈናቀለው አርሶአደር ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሲሆን አርሶ አደሮችም ህፃናት ልጆችን ይዘው ወደ ጐዳና ወጥተዋል። አንዳንድ አርሶአደሮች በሚዛን ተፈሪ፣ በጅማ፣ በአንቦ እና በአዲስ አበባ ሸክም በመሸከም እና ያለመጠለያ ከሰው እጅ እየለመኑ እንዲኖሩ ተገድደዋል።

በቅርቡ በእጃችን በደረሰን ሰነድ መሠረት ቁጥራቸው ከፍተኛ አርሶ አደሮች መሬታቸውን ተነጥቀው የአካባቢው ታጣቂዎች በጫረታ ስም እየተቀራመቱት ሲሆን አርሶአደሮችም አካቢውን በታጠቁ ሀይሎች አስገዳጅነት እንዲለቁ ሲደረግ በአሁኑ ወቅት አብዛኛዎቹ የአካቢው ነዋሪዎች የት እንደደረሱ አይታወቅም።

በጉራፋርዳ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው ስቆቃ የቀጠለ ከመሆኑም በላይ በ28/04/05 ዓ.ም ምሽት ላይ በጉራፋርዳ ወረዳ በበርጂ ቀበሌ ውስጥ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ስንዴ ስጦታው

ከወረዳው በታጠቁ አምስት ወታደሮች ግቢያቸው ውስጥ በመግባት በጥይት ደብድበው ገድለዋቸዋል። ወ/ሮ ስንዴ ስጦታው የስምንት ልጆች እናት ሲሆኑ ዛሬ ልጆቻቸው ያላሳዳጊ ቀርተዋል።

በተጨማሪም በ15/05/05 ዓ.ም የ7 ዓመት ልጅ የሆነችው ወርቂቱ ዳርካ በም/ቤት መኪና ተገጭታ መሞቷ በአካባቢው ህጻናት ላይ በተጀመረው ጥቃት አንዱ ማሳያ ሲሆን በዚሁ እለት 15/05/05 ዓ.ም እድሜዋ 4 ዓመት የሆነ የአቶ ክንዱ ልጅ በዚሁ ም/ቤት መኪና ተገጭታ መሞቷ በጉራፋርዳ ህዝብ ላይ እየተካሄደ ያለው ጥቃት ወደ ከፋ አቅጣጫ እና ወደ ዓለም አቀፍ ከባድ ወንጀልነት እየተቀየረ ነው። በ21/05/05 ከለሊቱ 8፡00 ሰዓት ከወረዳው መስተዳደር የተላኩ አራት ወታደሮች ወደ አቶ ይበሉ ማሞ ጊቢ በመግባት ሁለት በሬዎችና ሦስት በጐችን ወስደዋል። በአሁኑ ወቅት 32 ሰዎች በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ያለክስ እና ፍርድ እየተሰቃዩ ይገኛሉ።

በጉራፍርዳ ህዝብ ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ እየተካሄደ ያለው ወከባ እስራት እና ግድያ በአገራችን ታይቶ የማይታወቅ ሰባዊ እረገጣ እና የአንድን ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብን የማጥፋት ዘመቻ ሲሆን ኢህአዴግ እያካሄደ ያለውን አገርን የመከፋፈል እና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ዘመቻ አንድ አካል ነው። ከአካባቢው ነዋሪዎች እንደተረዳነው የታሰሩት ሰዎች የተጠየቁት የመኢአድ አባል እንደሆኑ እና ከአካባቢው መልቀቅ እንዳለባቸው አለበለዚያ ግን ሁሉንም እንደሚገኗቸው የወረዳው አስተዳዳሪዎች እና የፖሊስ ሀላፊዎች መግለጻቸው እንደዚሁም በጥር 3 ቀን 2005 ዓ.ም በቤንቺ ማጂ ዞን ሚዛን ተፈሪ ከተማ የዞኑ የመሬት አስተዳደርን በደብዳቤ የተጠየቁ የጉራፋርዳ ከተማ ነዋሪዎች የመሬት አስተዳደሩ ማመልከቻቸውን ተቀብሎ በመወርወር እናንተ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ደጋፊ በመሆናችሁ መኢአድ መሬት ይስጣችሁ ከእናንተ ጋር አንነጋገርም በማለት መፎከሩ ከላይ ላነሳነው የኢህአዴግ አስተሳሰብ ዋና መገለጫ ነው።

በጉራፋርዳ ላይ ለሚካሄደው ጥቃት የወረዳው መስተዳድር አቶ መሪሳ ጉጂ እና የአካባቢው የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ከበደ ለከቾ ከፍተኛውን ኃላፊነት እንደሚወስዱ ከአካባቢው አባላቶቻችን የደረሰን መረጃ ያመለክታል። ይህ ድርጊት በአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ላይ የተካሄደውን የሌሎች የአንዳንድ ሀገራት የዘር ማጥፋት ድርጊት ወደ አገራችን መግባቱን ያመለክታል።

ውድ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን በህዝባችን ላይ እየደረሰ ያለው ሰቆቃ የማንኛውም የሰው ፍጡር ላይ መድረስ የማይገባው ሲሆን በጉራፋርዳ ወረዳ ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ግድያ፣ እስራት፣ መሬት ማፈናቀል እና ድብደባ ለማስቆም ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ጋር በመሆን በጋራ ከፍተኛ ህዝባዊ ትግል ማድረግ የሚጠበቅብን ሲሆን በማንኛውም ኢትዮጵያዊያን ላይ እየደረሰ ያለ ግፍና መከራ ነገ በማናችንም ላይ ሊደርስ የሚችል በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጉዳዩን በትኩረት ሊከታተለው ይገባል።

በመጨረሻም ህዝባችን በደምና አጥንቱ በገነባው ሀገር የወለዳቸውን ልጆቹን እንኳን በላቡ ሰርቶ እንዳይኖር የሚያርሰው መሬት ከመንጠቃቸውም በላይ በጥይትና በዱላ በመደብደብ የጉዳና ነዋሪ እንዲሆን ሲፈረድበት መላው ኢትዮጵያውያን ከዳር ቆሞ ማየት የትውልድና የታሪክ ተወቃሽ ከማድረጉም በላይ ለህሊና እረፍት አይሰጥም። ስለሆነም ይህንን ጉጠኛ እና መንደርተኛ ቡድን በቃህ ብለን ሀገራችንን የሰቆቃ መንደር ከማድረግ ልንታደጋት የምንችልበትና መከላከል የሚገባን ቀን ዛሬ ነው። ስለሆነም መላው ህዝባችን ህብረብሔራዊ እና የሁሉም የኢትዮጵያውያን ፓርቲ ከሆነው ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ጉን በመቆም የህዝባችንን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት የመሬትና የፍትሕ ባለቤትነት ማረጋገጫ መታወቂያ ለኢትዮጵያውያን ልንሰጠው ይገባል።

በተባበረ ክንድ ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችንን እናስከብራለን!!

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/

ጥር 23 ቀን 2005 ዓ.ም